# ብ/ጀነራል ዮሃንስ ወልደማሪያም - በተጠባባቂነት አራተኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይል አዛዥ

ምንጭ - የኢትዮጵያ አየር ኃይል ታሪክ (1921 – 1983)



ብ/ጀነራል ዮሃንስ ወልደማሪያም ጥር 14 ቀን 1925 ዓም ወለጋ ክ/ሃገር ነቀምቴ ከተማ ተወለዱ ። ጀ/ል ዮሃንስ የአባታቸው የቅርብ ምክርና አስተማሪ በማግኘት ያደጉ አስተዋይ መኰንን ነበሩ ። ጀ/ል ዮሃንስ በአእምሮም ሆነ በሰውነት ንቁና ስፖርት አዘውታሪ መኰንን ነበሩ ። አባታቸው ስለትምህርት በነበራቸው በጐ አመለካከት ታንፀው ያደጉ ወጣት ነበሩ ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በስዊዲሽ ኢቫንጀሊካል ሚሽን ተምረዋል ። ወጣት ዮሃንስ አገር ቤት የሚሰጣቸውን ትምህርት እንዳጠናቀቁ ወደ ስዊድን አገር ተልከው ቄስ እንዲሆኑ ስዊድናውያን ሚሽነሪዎች በማዘጋጀት ላይ ነበሩ ። ተማሪ ዮሃንስ ቀጥለው ወደ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተዛውረው ለሁለት ዓመታት ተምረዋል ። የወጣቱ ዮሃንስ ወልደማሪያም የአየር ኃይል ሕይወት የጀመረው በ1941 ዓም በራዲዮ ኦፕሬተርነትና በናቪጌተርነት ሲቀጠር ነው ። ከዚያም ካዴት ዮሃንስ ባሳየው የትምህርት ብቃትና ወታደራዊ ሥነምግባር አክባሪነት ወደ በረራ ትምህርት ቤት ተዛውሮ አውሮፕላን ማብረር ተማረ ።

ብ/ጀ ዮሃንስ በበረራ ሥልጠናና በክፍል ትምህርት በተደጋጋሚ ከጓደኞቻቸው ልቀው በመገኘታቸው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እጅ የወርቅ ሰዓት ተሸልመዋል ። በ1945 ዓም የም/መ/አለቅነት ማዕረግ አገኙ ። በከፍተኛ ችሎታቸውና ምግባራቸው ምክንያት በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች እየተመደቡ በቅን አገልግለዋል ። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል

- በበረራ አስተማሪነት
- በስኳድሮን አዛዥነት
- የኤፍ-5ኤ ሱፐር ሶኒክ ስኳድሮን መስራችና አዛዥ
- የጀት በረራ ማሰልጠኛ ስኳድሮን አዛዥና አስተማሪ

ሆነው አገልግለዋል ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከብዙ ዓመታት የሥራ ልምዳቸው በተጨማሪ አሜሪካን አገርና እንግሊዝ አገር እየተላኩ ከፍተኛ የአዛዥነት ኰርሶች ወስደዋል ። አሜሪካን አገር በሚገኘው አየር ዩኒቨርሲቲ

- የስኳድሮን አዛዥነት ኰርስ
- የጀት በረራ ስልጠና “ራንዶልፍ” አየር ኃይል ጣቢያ
- የኤፍ-86 ተዋጊ አውሮፕላን በረራ “ሉክ” አየር ኃይል ጣቢያ
- የኤፍ-5 ተዋጊነት ሥልጠና “ዊልያምስ” አየር ኃይል ጣብያ (አሪዞና)




በሚገባ አጠናቀዋል ። የከፍተኛ ዕዝና ስታፍ ኰሌጅ ትምህርታቸውን እንግሊዝ አገር ሮያል ኤር ፎርስ አጠናቀዋል ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ብ/ጀ ዮሃንስ በውትድርና ሕይወታቸው ተመድበው በሰሩባቸው ክፍሎች ሁሉ ያስገኟቸው ውጤቶች እጅግ የሚደነቁና የሚያኰሩ ናቸው ። በላቀ ሥራቸውና በምግባራቸው ከደረሱባቸው ደረጃዎች ዋነኞቹ -

- ምክትልና ተጠባባቂ የአየር ኃይል አዛዥ (ለአጭር ጊዜ)
- የመከላከያ ሚ/ር አማካሪ (ለአጭር ጊዜ)
- በዋሽንግተን ዲሲ የኢትዮጵያ መከላከያ አታሼ

ሆነው አገልግለዋል ።



መኰንኑ በሥራቸውና በወታደራዊ ሥነ ስርዓታቸው በምሳሌ የሚጠሩ ነበሩ ። በአየር ኃይል የዕድገት መሰላል እጅግ በተሳካ ሁኔታ እየተመሰገኑና እየተሸለሙ ያደጉ መኰንን ነበሩ ። በአስተማሪነት ፣ በተዋጊነትና በአዛዥነት የላቀ አገልግሎት ያበረከቱ መኰንን ናቸው ። ኤፍ-5 የተባለውን ተዋጊ አውሮፕላን አየር ኃይሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲረከብ ጀነራል ዮሃንስና ኰ/ል ጥግነህ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ኃብተ ጊዮርጊስ የመጀመሪያዎቹ ሰልጣኞች ሆነው ወደ አሜሪካን አገር እንዲሄዱ ተደረገ ። ጀነራሉ ያን ጊዜ ለሥልጠናው የተላኩት አውሮፕላኑን በረው በመምጣት ሌሎችን እንዲያሰለጥኑ ብቻ ሳይሆን የስኳድሮኑም አዛዥ እንዲሆኑ ታስቦ ነበር ። እ.አ.አ በ1974 ዓም ኢትዮጵያ ውስጥ የፈነዳው አብዮት ለብዙዎቹ በችሎታቸውና በዕውቀታቸው ምስጉን ለሆኑ የአየር ኃይል መኰንኖች መቅሰፍት እንደሆነው ሁሉ ጀ/ል ዮሃንስም የዚሁ ችግር ሰለባ ሆነው በስደት እንዲኖሩ አስገድዷቸዋል ። መኰንኑ የአየር ኃይል አዛዥ ሆነው ለማገልገል ችሎታውም ሆነ ልምዱ እንደነበራቸው ምንም ጥርጥር የለውም ።

በ1969 ዓም ዋሽንግተን ዲሲ ወታደራዊ አታሼ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ መንግስት ለምክክር ወደ አዲስ አበባ ሴጠራቸው ጥሪውን ሳይቀበሉ አሜሪካን አገር የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቀው አሜሪካዊ ዜጋ በመሆን አዲስ ኑሮ ጀመሩ ። በዚያን ጊዜ ነው የውትድርና ዓለሙን ትተው አዲሱንና የተሳካውን የሲቢሉን ሕይወት የጀመሩት ። አዲሱ ሕይወታቸው ወደ ንግዱ ዓለም አስገብቷቸው ከ1969 እስከ 1974 ዓም ድረስ የኖርትሮፕ ፣ የዌስትሃውስና ስፔሪ/ዩኒቬአ ማርኬቲንግ ኰንሰልታንት ሆኑ ። ቀጥለውም እ.አ.አ ከ1982 እስከ 1986 ዓም ድረስ የኖርትሮፕ ማርኬቲንግ ዳይሬክተር ሆነው ሰርተዋል ። ከዚያም ከ1979 እስከ 1984 ዓም ድረስ ፓናልፒና ኤፍ.ኤም ኤስ ኢንክ የተባለው ኢንተርናሽናል ዕቃ አጓጓዥ ኩባንያ ፕሬዝዳንት ሆነው ሰርተዋል ። የንግድ ሥራ እንቅስቃሴያቸው ቤተሰባቸውን ፣ በቅርብ የሚያውቋቸውን ጓደኞቻቸውንና ወዳጆቻቸውን እንዲረዱ ዕድል ሰጥቷቸዋል ።

ጀ/ል ዮሃንስ በእግዚአብሄር ያላቸውን ዕምነት ያልረሱና ልዩ ሰው ስለነበሩ ያጡና የተቸገሩን ለመርዳት ያላቸው ፅኑ እምነት አፅንቶላቸዋል ። ስለሆነም ሪሊፍ ሰርቪስ ቻሪቲስ (የእርዳታ አገልግሎች) ለተባለው ዕርዳታ ለጋሽ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በበጐ ፈቃድ የቦርድ አማካሪ አባል ሆነው ለስድስት ዓመታት ሰርተዋል ።

ከዚያም ከ1991 ዓም ጀምሮ የዚሁ ድርጅት የቦርድ አባል ሆነው በማገልገል ላይ ነበሩ ። እንዲሁም “ብሬድ ኤንድ ወተር ፎር አፍሪካ” ለሚባለው ሌላ መንግስታዊ ያልሆነ በጐ አድራጐት ድርጅት የቦርድ አባል ነበሩ ። በዚህ ድርጅት አማካኝነት አፋርና ኦሮሚያ ውስጥ አገር ውስጥ የሚገኙ የሌሎች ድርጅቶችን አገልግሎት በመጠቀም ዕርዳታ እንዲደርስ አድርገዋል ።

እኒህ ደግ መኰንን ለሰው ያላቸው ርህራሄ ከልጅነታቸው ጀምሮ ከአባታቸው ከወረሱት የክርስቲያን መንፈስ እንደመነጨ ደጋግመው ያነሱ እንደነበር ታውቋል ። አባታቸው ያለቻቸውን ትንሽ ነገር ለተቸገሩና ለአካለ ጐዶሎዎች ያካፍሉ እንደነበርና ጀነራሉም ይህን ደግነት ከአባታቸው ወርሰው ለተቸገሩ ያላቸውን ሰብዓዊ ርህራሄ ሁልጊዜ በተግባር ያሳዩ እንደነበር ታውቋል ።

ብ/ጀ ዮሃንስ ሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓም ከጓደኞቻቸው ጋር ሆነው ሲጫወቱ በልብ ሕመም በድንገት ሕይወታቸው አልፎ ሥርዓተ ቀብራቸው በጴጥሮስ ወፓውሎስ ቤተ ክርስቲያን ተፈፅሟል ። ከወ/ሮ ወይንሸት ጋር ተጋብተው ያፈሯቸውና አሜሪካን አገር ኑሯቸውን መስርተው የሚኖሩ ሶስት ልጆች አሏቸው ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com